አጠቃላይ የሽያጭ ስምምነት

ትርጉም

ስምምነት፡- በደምበኛው እና በቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የተፈረመውን የካርድ / ካርዶች / አቅርቦት ስምምነትን ይመለከታል ።

ደምበኛ፡- ከቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ጋር ይህን ስምምነት የተፈራረመው አካል ወይም ግለሰብ ማለት ነው ።

ወኪል፡- የቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ካርድን ለመጠቀም በደምበኛው ሙሉ ስልጣን የተሰጠው ሰው ማለት ነው ።

ካርድ፡- ደምበኛው በስምምነቱ ላይ የተጠቀሱትን ምርቶች ለመግዛት የሚችልበት ተቀባይነት ያለው የቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ካርድ ማለት ነው ። ይህ ካርድ በማንኛውም አይነት መንገድ ጥሬ ገንዘብ ለማግኘት ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም ።

ምርት፡- ደምበኛው ከተፈቀደለት ገደብ ሳያልፍ በቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ማደያዎች በካርድ አማካይነት የሚገዛቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ማለት ነው።

የመሸጫ ቦታ፡- የካርዱ አገልግሎት ለመስጠት የተፈቀደበት/ የሚችል የቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. መለያ ቀለማት ያለበት ማደያ ማለት ነው ።

የሚስጥር ኮድ፡- በደምበኛው የተመረጠ ወይም ከቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የካርድ ዝግጅት ሲስተም የሚሰጥ አራት አሃዝ የያዘ መለያ ቁጥር ማለት ነው ።

የኤሌክትሮኒክ የቅድሚያ ክፍያ ካርድ፡ በቅድመ ክፍያ ዘዴ የሚሰራ ካርድ

አንቀፅ አንድ፡ አላማ

ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ደምበኛው ምንም አይነት ቀጥታ ክፍያ መፈፀም ሳያስፈልገው ምርቶችን መግዛት የሚችልበት አቢሲኒያ ካርድ የሚባል የመግዣ ካርድ ለደምበኛው ያቀርባል። ደምበኛው በመሸጫ ቦታዎች የሚሸጡ፣ በቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የተፈቀዱ እና ካርዱ ለደንበኛው በሚሰጥበት ጊዜ ለደምበኛው በዝርዝሩ የተመለከቱ የምርት አይነቶች እና መሸጫ ቦታዎች መግዛት የሚችልበት ነው ። እንዳስፈላጊነቱ በዝርዝሩ ላይ ማሻሻያ ሊደረግበት ይችላል ። ይህም ዝርዝር በደምበኛው ጥያቄ መሰረት ሊሰጠው ይችላል ።

አንቀፅ ሁለት ፡ የካርዱ አጠቃቀም

የአቢሲንያ ካርድ አጠቃቀም ፡-

- በስምምነቱ በተዘረዘሩት እና ደምበኛው በተስማማባቸው ግዢታዎች ውስጥ ከተፈቀደውና ከተገለፀው የምርት አይነት እና ልክ ሳያልፍ ለደምበኛው እና/ወይም ለወኪሎቹ መጠቀሚያ የተወሰነ ይሆናል ።
- ደምበኛው የመሸጫ ቦታዎችን ዝርዝር በጥያቄ ከካርድ ሽያጭ ክፍል ማግኘት ይችላል ።
- አጠቃቀሙ በጊዜ ገደብ የተወሰነ ይሆናል /ማለትም በስምምነቱ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ገደብ መሠረት/
- ማንኛውም ግብይት ከመፈፀሙ በፊት ደምበኛው ለማይያው ሰራተኞች ካርዱን ማሳየት አለበት ።
- ካርዱ የተፈፀመ ማንኛውም ግብይት ከካርድ መቀበያው መሳሪያ ላይ በሚታተም ደረሰኝ ማስረጃ ይጠናቀቃል::
- እያንዳንዱ የግብይት ሂደት በሚፈፀምበት ጊዜ ደንበኛው በካርድ መቀበያ መሳሪያው ላይ የሚያስገባው የምስጢር ኮድ ደምበኛው ግብይቱን ለመቀበሉ እንደ ፊርማው ሆኖ ያገለግላል::
- ከእያንዳንዱ የግብይት ሂደት በኋላ ከካርድ መቀበያው መሳሪያ ላይ ታትሞ የ ወጣው ደረሰኝ ለተደረገው ግብይትና ክፍያ ማስተባበያ የሌለው ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል። ደምበኛው በካርድ በቀን እስከ ስድስት ጊዜ ግብይት መፈፀም ይችላል።
- የነዳጅ ግብይቱ የመኪናው ነዳጅ ጋንን በቀጥታ ለመሙላት ብቻ የተወሰነ ሲሆን ከዚያ በኋላ በማንኛውም መንገድ ከመኪናው ነዳጅ ጋን የገባውን ማውጣትን አይመለከትም::

አንቀፅ ሶስት ፡ የካርዱ ባህርያት

በስምምነቱ መሰረት ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የተፈቀዱት የምርት አይነቶች ዝርዝር እንዲሁም በሌላ መንገድ ካልተገለፀ በስተቀር የመኪናው የሰሌዳ ቁጥር እና/ወይም የደንበኛው ስም የታተመበትን ካርድ ደምበኛው በጠየቀው ብዛት መሰረት አዘጋጅቶ ይሰጣል ።

ለእያንዳንዱ ካርድ የሚስጥር ኮድ ይሰጠዋል። ካርዱን መጠቀም የሚችለው ይህንኑ የሚስጥር ኮድ የሚያውቀው የካርዱ ባለቤት ብቻ ይሆናል ። ደምበኛው ካርዶቹን ከሚስጥር ኮዱ /ኮዶቹ/ ጋር አንድ ላይ ማስቀመጥ የለበትም፣ የተሰጠው የሚስጥር ኮድ በሚስጥር መያዝ

አለበት። ስምምነቱ በተፈረመበት ቀን በሚሰራበት ይፋ የካርድ የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር መሠረት ለየአንዳንዱ ካርድ

ክፍያ ደንበኛው ይጠየቃል። ለደምበኛው ለመክፈሉ ደረሰኝ ተሰርቶ ይሰጠዋል ። በደምበኛው በታዘዘው የካርድ ቁጥር መሰረት የነጠላ ካርድ ዋጋ ሊቀያየር ይችላል ። በማንኛውም ጊዜ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሳያስፈልግ በዋጋው ላይ ማሻሻያ ሊደረግበት ይችላል ። /በቀላል ጥያቄ የዋጋ ዝርዝር ማግኘት ይቻላል/ ።

በደምበኛው የሚጠየቀው እያንዳንዱ በካርድ ላይ የሚደረግ ለውጥ በቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ያለምንም ክፍያ ይሰራለታል።

አንቀፅ አራት ፡ ዋጋ ማስከፈያ እና የክፍያ አሰባሰብ የክፍያ መጠየቂያ

ግዢ የተደረገባቸው የምርት አይነቶች በስምምነቱ ላይ በተወሰነው የጊዜ ገደብ መሰረት ግብይቱ በተፈፀመበት እለት የመሸጫ ቦታዎች በሚያስከፍሉት ዋጋ መሠረት ይከፈልባቸዋል። በየጊዜው ለደንበኛው በሚቀርቡት የክፍያ መጠየቂያ ሰነዶች ላይ የሚጠቀሱትን ክፍያ እና የግብይት አይነት በተመለከተ ሊነሱ የሚችሉ ማንኛውም ቅሬታ ወይም አለመግባባት የክፍያ መጠየቂያው በተሰጠበት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ደንበኛው ከማስረጃ ሰነድ ጋር ተያይዞ በፅሑፍ መቅረብ አለበት። ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም ።

ክፍያ

ክፍያው በስምምነቱ በተመለከተው የክፍያ ግዴታ እና ቀን መሠረት መፈፀም አለበት። የቅድሚያ ክፍያ ካርድን በተመለከተ ሶስት አይነት የአሞላል (recharge) ዘዴዎች አሉ ። በቀጥታ በማይያው ላይ በደምበኛው የሚጠየቀው ዋጋ የሚሞላበት አሰራር (ይህን አማራጭ ባሁኑ ጊዜ ማግኘት የሚቻለው በተመረጡ ማይያዎች ላይ ብቻ ነው) ። በሚሞላበት ጊዜ በደንበኛው የሚገባው የሚስጥር ኮድ ግብይቱ ተቀባይነት ለማግኘቱ ማስረጃ የደምበኛው ፊርማ ሆኖ ያገለግላል። ሁለተኛ ደግሞ ደምበኛው ካርዱን በቀጥታ ወደ ቶታል የካርድ አገልግሎት ክፍል በማምጣት ክፍያውን ፈጽሞ ካርዱን አስሞልቶ የሚሄድበት ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ የቅድሚያ ክፍያውን በቶታል የካርድ አገልግሎት ክፍል በመክፈል ከ48 ሰአት በኋላ በማንኛውም ማደያ ላይ በመሄድ የተከፈለበትን መጠን ደንበኛው ፒን ኮድን በማስገባት የሚያስሞላበት ዘዴ ነው።

ከክፍያ አስቀድሞ የሚቀርብ ማንኛውም የማስሞላት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም። ክፍያ መጠየቂያው ላይ በተጠቀሰው ቀን ማንኛውንም ክፍያ መፈጸም አለመቻል ያለምንም መደበኛ ማስጠንቀቂያ በቀጥታ ለእያንዳንዱ ላልተከፈለበት ቀን ባልተከፈለው ዋጋ መጠን በወር 2 በመቶ የወለድ መቀጫ ያስከትላል።

በከፊል ክፍያ በሚፈጸምበት ወይም በማይከፈልበት ጊዜ ያለምንም ማስጠንቀቂያ እና ያለፍርድ ቤት ውሳኔ በቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. በሚሰጥ ማስጠንቀቂያ ብቻ ይህ ስምምነት ወዲያውኑ ይቋረጣል።

አንቀጽ አምስት ፡ ስምምነቱ ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ ስምምነት የተደረገው በስምምነቱ ላይ ለተወሰነው የጊዜ ገደብ ብቻ ነው፡፡ በእንደኛው ወገን ካልተሰረዘ በስተቀር በጋራ ስምምነት ሊራዘም ይችላል። ካርዱ ለደምበኛው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአገልግሎት ላይ ይውላል። እያንዳንዱ ወገን ስምምነቱ ከመሰረዙ በፊት ቢያንስ የስምንት ቀን ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ በመስጠት ይህን ስምምነት በማንኛውም ጊዜ የመሰረዝ መብት አለው። ካርዱ የቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ንብረት በመሆኑ በማንኛውም ምክንያት ይህ ስምምነት በሚቋረጥበት ጊዜ ደምበኛው ወዲያውኑ ለቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ካርዱን ይመልሳል፣ እንዳይጠቀምበትም ይታገዳል። ስምምነቱ ከተቋረጠ በኋላ ደንበኛው ካርዱን ለመጠቀም የሚቀጥል ወይም የሚሞክር ከሆነ በሕግ ይጠየቃል ካሳም እንዲከፍል ይገደዳል።

አንቀጽ ስድስት ፡ የደምበኛው ግዴታ

ካርዱ ሙሉ በሙሉ በአደራ ለደምበኛው ይሰጣል። ሆኖም ካርዶቹ በሶስተኛ ወገን እንኳን ጥቅም ላይ ቢውሉ የደንበኛው ኃላፊነት ነው።

ደንበኛው በካርዶቹ ለተፈጸመው ማንኛውም ግብይት ከስምምነት ውጪ የሆነ ግዢ እንኳን ቢፈጸም ለቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የመክፈል ግዴታ አለበት።
ደምበኛው ማንኛውንም ለውጥ /አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ ፋክስ፣ እና ከቀጥታ ተቀናሽ ክፍያ ጋር የተያያዘ ማንኛውም የባንክ መረጃ/ በጽሑፍ ለቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

ስምምነት የተደረገበትን የክፍያ የጊዜ ገደብ ግምት ውስጥ በማስገባት ከእለታዊ እና ከወርሃዊ የግብይት መጠን የተፈቀደው የእለታዊ ግዢ ቁጥር ገደብ በስምምነቱ ላይ ይገለጿል።

አንቀጽ ሰባት ፡ ካርድ /ዶች/ ቢጠፉ ወይም ቢሰረቁ

አንድ ወይም ከአንድ በላይ ካርድ በሚጠፋበት ወይም በሚሰረቅበት ጊዜ ደምበኛው በሚቀጥለው የ48 ሰአት ጊዜ ውስጥ ወዲያውኑ በስልክ /በቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የሥራ ሰአት/ ወይም በፋክስ በጽሑፍ ማረጋገጫ ጉዳዩን ለቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

ሆኖም ማሳታወቂያ ከተሰጠ በኋላ በ48 ሰአት ጊዜ ውስጥ በጠፋ ወይም በተሰረቀ ካርድ ለሚደረግ ለማንኛውም አይነት ግብይት ተጠያቂነቱ የደምበኛው ይሆናል።

የጠፋ ወይም የተሰረቀ ካርድ ቢገኝ ደምበኛው በጽሑፍ ጥያቄ ሳያቀርብ እና ከቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ሳይፈቀድለት ካርዱን ሊጠቀምበት አይችልም።

ካርዱ ከጠፋ ወይም ከተሰረቀ በኋላ ደምበኛው ለቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ካሳሳወቀ ወይም የ48 ሰአት የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ቢያሳውቅ ደምበኛው ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል።

አንቀጽ ስምንት ፡ ስለ ካርዱ መሰረዝ

ደምበኛው የስምምነት ግዴታውን ከጣሰ ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ደምበኛው የያዘውን ካርድ እንዳይጠ ቀምበት ወዲያውኑ ሊያስቆም ይችላል።

ደምበኛው አንድ ወይም ካንድ በላይ ካርድ እንዲሰረዝለት በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል። ካርዶቹንም ለቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. መመለስ ይኖርበታል።

ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. የአንድ ደምበኛን ካርድ መሠረዝ እና/ወይም እድሳት መከልከል ይችላል። ይህ ውሳኔም ለደምበኛው በጽሑፍ መገለጽ ያለበት በደምበኛው የገንዘብ አቋም ላይ የተደረገውን ማንኛውንም ጉልህ ለውጥ፣ የዋስትና ተቀማጭ እና/ወይም የባንክ መያዣ አለመኖርን ወይም በቂ አለመሆንን፣ ያልተከፈለ ቀሪ ክፍያን እና ያልተለመደ ግዢን፣ ከተፈቀደው ገደብ በላይ የተሸጡ ምርትን፣ ወዘተ ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

አንቀጽ ዘጠኝ ፡ የአጠቃላይ ሁኔታ

ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. በዚህ ስምምነት ግዴታ ላይ በማንኛውም ጊዜ ማሻሻያ ወይም ጭማሪ ማድረግ ይችላል። ደምበኛው የተገለው የጽሑፍ ሰነድ ከደረሰው በኋላ ማንኛውንም ግዢ ሲፈጽም ደምበኛው የአዲሱን ስምምነት አንቀጾች እንደተቀበለ ይቆጠራል።

አንቀጽ አስር ፡ ከቁጥጥር ውጪ የሆኑ አስገዳጅ ምክንያቶች

ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ. ከቁጥጥር ውጪ በሆኑ አስገዳጆች ምክንያት ግዴታውን መወጣት ባይችል ከተጠቀሱት ነጻ ይሆናል። ይህም ከቁጥጥር ውጭ የሆነ አስገዳጅ ምክንያት በሕግ ከተወሰነው ውጪ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡ ጦርነት፣ የሥራ ማቆም አድማ፣ የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት አቅርቦት ወይም የማጓጓዣ ሁኔታን የሚያስናክሉ ሁኔታዎች ወይም በገበያ ላይ የሚውለውን የምርት መጠን የሚገድብ ሁኔታ ወይም በሽያጭ ላይ ገደብ የሚያስከትል ሕግ ሲኖር ነው::

አንቀጽ አስራ አንድ ፡ ዳኝነት

የዚህን ስምምነት ትርጉም ወይም የግዴታ አፈጻጸም በሚመለከት ሊነሳ የሚችል ማንኛውም ክርክር የሚገዛው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ይሆናል። የሚዳኘውም በቶታል ኢትዮጵያ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት በአዲስ አበባ በሚገኝ አግባብ ባለው ፍርድ ቤት ይሆናል።

TOTAL